ጠላው አልበጀ ቅራሪው ሰው ፈጀ

ከበልጅግ አሊ

የግንቦቱ ምርጫ የወያኔ ከፍተኛ የፖለቲካ ክስረት አጎልቶ በአለም ከአሳየ በኋላ ወያኔ ያንን ለማስተካከል ከፍተኛ የሆነ ጥረት ላይ መሆኑን እናያለን። ወያኔ ጥቂት ሆዳሞችን እንደየፍላጎታቸው እያባበለ ደጋፊዎቹን ለማብዛት ጥረቱ በከፍተኛ ሁኔታ ተያይዞታል። ኋሆዳሙን በሆዱ፣ ጉረኛውን በማሞገስ ፣ ደካማውን መስፈራራት፣ ይሆንልኛል ብሎ ድንጋዩን ሁሉ መፈንቀል ይዞአል። በተለይ በውጭ ሃገር የሚገኙትን ለጥቅም ተሯሯጭ ግለሰቦችን በገንዘብና በከተማ ቦታን በመስጠት ተራና ተልካሻ የሆነ ጥረቱን ተያይዞታል። ወደ አገራችን ስንሄድ ደግሞ ሁኔታው የተለየነው። የሃገሪቱን ሕዝብ ግን የግንቦቱ ምርጫ ምርኮኛ አድርጎ በጅምላ በአጋዚ ጦር እየጨፈጨፈ እንቢ ያለውን በማስፈራራት፣ የጠነከረበትን በመግደል፣ የቅንጅት መሪዎችን በማሰር፣ የኢሕአፓ አባለትን በመግድል፣ መድረሻቸውን በማጥፋት ፣ ለደጋፊዎቹ መንግስተ ሰማያት ለተቃወሚዮቹ ደግሞ ጋህነብ እሳት የሆነች አገር እየፈጠረ ነው። ሆዳሞች የዛችን ሃገር ህዝብ ሰቆቃ መንገድ እየፈለጉ በቆንጆ መልኩ ሊያሳዩን ይሞክራሉ። የወያኔ ቅጥረኞች የኢኮኖሚውን እድገት አሳድገው ከጃፓንም ከጀርመንም እያሰበለጡት ነው። የሃገሪቱ ኢኮኖሚ አደገ የሚሉን ውሃ በአዲስ አባባ በተራ በሚታደልበት ግዜ፣ የስራ አጡ ቁጥር ሰማይ በነካበት ሁኔታ፣ ስንዴ በቤተሰብ በሚታደልበት ወቅት፣ እያለን ነው ።

አንዱ የሚያሾፉብን መንገድ ደግሞ ሚሌኒየም የሚባለው የበአል ዝግጅት ነው። ከዚሁ በተያያዘ በግለሰብ ደረጃ ለደጋፊዎቻቸውና አዲሰ ደጋፊነት ለሚመለመሉ ገንዘብ የሚገኙበትን ኮንትራት እየሰጡ ሆዳሞችን እየገዙ ነው። ነገ ሰለሞን ተካልኝ በሚሊየነሙ ውስጥ ቦታ ቢሰጠው ትንቢት ተናጋሪ ፃድቅ አያስብለኝም። ለወያኔ የማደሩን ምክንያት ሲገልፅ ከትግሉ በግል ጥቅም አላገኝሁበትም፣ በግልም አላተረፍኩበትም ብሎ ነበር የጀመረው። ለነገሩ እሳት ከሌለ ጭስ የለም እንዲሉ ሰለሞን ላይ የሚወራው አፈቃሪ ነዋይ ነው የሚባለውን ደካማ ጎኑን በመጠቀም ይሆን ወያኔ በእጁ ያስገባው? ለወያኔ ዛሬ ቆመው የምናያቸው እነ አበበ ባልቻም፣ እነ ሙሉጌታም ፣ እነ ስዩምም እንደዚሁ አፍቃሮተ ነዎይ እንዳለባቸው ወይም በመጥፎ ጠባይ የተነደፉ መሆናቸው የታወቀ ነው። ሌሎችም ገና በየፈርማታው በግል ትርፍ በሚያገኙበት ሁኔታ እያስተካከሉ ከትግል መድረኩ ቢወርዱ ሊደንቀን አይገባም።

የሰለሞን ተካልኝ ወደ ወያኔ መዞር ብዙዎቹን ሰዎች አስደንቋል። እኔንም ውሸት ምን ያደርጋል ትንሽ ደንገጥ አርጎኝ ነበር። ወዲውኑ እኔና እኔ ስንሞገት አይ በልጅግ ለካ በዚህ በተልካሻ ሰው ጥሩምባ ተደልለህ ነበር ብሎ ህሊናዬ ወቀሰኝ። የስንት አመት የከሃዲዎች ልምድ እንደሌለኝ ይህ እንደገና ሊያስደነግጠኝ ባልተገባ ነበር። በተለይ ሰለሞን ድሮም ቢሆን አንዳንዶቹ ዘፈኖቹ ቅጥ ያጡ ነበሩ ። ጠላውም አልጠቀመ ቅራሪው ሰው ፈጀ ማለት ይህ ነው።

የኢትዮጵያ ህዝብ አንድ ነገር መጠበቅ አለበት። ሰለሞን የመጀመሪያው ሲሆን ነግ ተነገ ወዲያ ታላላቅ የፖለቲካ መሪዎች ሳይቀሩ ይህንን ለወያኔ ማደር ክህደት ቢፈፅሙ ምንም ሊደንቀን አይገባም። የነበረ፣ ያለና፣ የሚኖርም ነው። „ማንዴላ“ ልድቱ (ክህደቱ)ን፣የህብረቱ ዶክተሮችን ማስታወስ ይበቃል። ንዋይ፣ የስልጣን ጥማት፣ የትግል መራዘም ፣ የመንግስት አረመኔነት ሁሉም በየተራቸው አስተዎፅኦ እያደረጉ የተልካሾችን ልብ እያስካዱ አጎብዳጅ እንዲሆኑ ያደርጓቸዋል። ነግ ተነገ ወዲያ ደግሞ ሌሎች ግለሰቦች ለትግሉ ያደረጉትን አስተዋፅኦ ሁሉ እርግፍ አድርገው ትተው ለአዲሱ አቋማቸው የሚስማማ ቲወሪ ይነድፋሉ ። ትግሉ ተራዘመ ፣ በሰላማዊ መንገድ

PDF created with pdfFactory trial version www.pdffactory.com

መታገል፣ የጡረታ መሬት እንመራ፣ ለመጪው ምርጫ እንዘጋጅ፣ በማለት ወያኔ በሚያወጣልን መመሪያ ሰር ተስማምተን እንስራ ብለው ይጎተጉቱናል። አንድ የማይረዱት ነገር ግን መሰረታዊ ለሆነ ለውጥ መታገላቸውን ትተው የግል ጥቅማቸው አንተርሰው ወያኔን ጠጋግነው ሊሄዱ መዘየዳቸውን የኢትዮጵያ ህዝብ እንደማይቀበላቸው ነው። ትግሉ እረዘመብን ካሉ እረፍት መውሰድ እንጂ ወያኔ ጋር መሄድ አያስፈልግም ወይም ደግሞ በሰላም ልታገል ካሉ ስንት በሰላም መታገል የሚፈልግ ተቃዋሚ እያለ በአደባባይ ስንት ሰላማዊ ወጣቶችን የገደለው ወያኔ ጋ መሄድ ምን አመጣው? ትግሉ ረዘመ ፣ ውጤት አጣ፣ የተቃወሚዎች ድል እራቀ ከማለትና ለወያኔ ከማደር ቆርጦ መታገል ለሁሉም መፍትሄ ይሆናል።

ጥቅም አይንን ይሸፍናል ፣ ህሊናል ያቃውሳል ፣ ይሉንታን ያሳጣል ፣ ሌላው እንደኔ አያስብም በሚል የጂሎች መፈክር እንደነ ሰለሞን አይነቶች ሊያወናብዱን ይሞክራሉ። ትንቢት ተናጋሪ ሆንክ አትበሉኝ እንጂ ሰለሞን በቅርብ ቀን ወያኔ ተጠቅሞ ሲጥለው የኢትዮጵያን ህዝብ ማየት፣ መድረክ ላይ ወጥቶ መዝፈን ፣ እስከሚያቅተው ድረስ የአፍረት ካባውን ይከናነባል። የሰለሞን ተልዕኮ ለሚሌኒየሙ ከውጭ ከሚገባውን ሰው በትልልቅ ሆቴሎች ከማስደሰት አያልፍም። ጥርሱ እንዳለቀ አንበሳ ሁሉም በሱ ላይ ሲነሳበት፣ ወያኔን በመቃወሙ ያገኘው ክብር ሞገሱ ተረሰቶ በአዲሳ አባባ ጎዳና ላይ፤ይህ በወያኔ የተሰቃየ ህዝብ የጥላችና ፊት ሲያሳየው **ሰለሞን ተካልኝ** ያ ታላቅ ሰው **የካሃዲነት ኒሻን** ከህዝብ ፣ ከወያኔ ደግሞ የባዶ **ሚሌኒየም ጀግና** ተሸላሚ ሆኖ ይቀራል ። ቀን ሲያልፍ ፣ የሚሌንየም በአል ሲያልፍ እኔ ሰለሞን ተካልኝን አያድርገኝ ጥላው የሚፈራ የወያኔ ካድሬ ሆኖ ይቀራል። እንደ ልደቱ (ክህደቱ) እሱም በአጋዚ ጦር ይጠበቃል። **አዲሱ ሰለሞን ተካልኝ ።**

ወያኔ አዲስ ባመጣው ፈሊጥ የተለያዩ ሙከራዎችን አድርጓል። ሶማሌም ገብቶ ለኢትዮጵያ ጥቅም ነውና ደግፉኝ ብሎአል። ሚሌኒይምን ልደግስ ነውና ተባበሩኝ ብሎአል። እነዚህ ሁሉ አልሰሩለትም ነበር። አሁን ደግሞ በኦጋዴን የተደረገው ጭፍጨፋ በትንሹም ቢሆን ሰርቶለታል። ነገ ከኤርትራ ጋር ጦርነት ሊከፍት ይችላል። አንድ የማይችለው ግን አንቀፅ 39 ቀይሮ ፣ የዘር ፓርዎችን አግዶ ፣ ክልልን አፍርሶ ፣ ከኢትዮጵያ ህዝብ መታረቅ ነው። ያንን አድረጎ ከጠርሙሱ ያወጣውን የዘረኝነት ጂኒ ወደ ጥረሙሱ እስካልከተተ ድርስ የምድረ ካሃዲ መክተልተለክ ምንም ፋይዳ ሰለማይኖረው ሙከራው ሁሉ አንዳንድ ቅን አንጀቶችን ያራራለት እንደሆን እንጂ ሌላ ምንም የረባ ለውጥ አያመጣለትም።

ለወያኔ ለማደር ለምትፈልጉት ሁሉ አንድ ቁም ነገር ልታውቁ ይገባል። ወደ ወያኔ መሄድ ቀላል ነው። ወያኔ ተጠቅሞ እንደ ኮካ ኮላ ጠርሙስ ሲጥላችሁ መመለሻው ግን የዘላለም ፀፀትና ውርደት ነው። ሀፍረት ነው። ከዚህ ሁሉ አስቦ ጠንቅቆ መወሰን ያስፈልጋል። በተለይ በስተርጅና በታሪካችሁ ላይ መጥፎ ጉድፍ እንዳታኖሩ አደራዬ የጠበቀ ነው።

በልጅግ አሊ

PDF created with pdfFactory trial version www.pdffactory.com

PDF created with pdfFactory trial version www.pdffactory.com